# የተስፋዬ ገብረ አብ ሁለተኛ ግንባር

## ኢ.ሕአፓን በመኢሶን - እሾህን በሾክ

ይቅር ደሞዜ

ባለፈው ጊዜ “የማታውቅባትን የሰው . . . “ በሚል አቶ (ብፃይ) ተሰፋዬ ገብረአብ በፓልቶክ ስለሰጠው የተሳሳተ መረጃ፣ ማለትም የአማራንና የኦሮሞን ሕዝብ ለማጣላት የፈጠረውን የትርጉም ስህተት ከበልጅግ አሊ ቀርቦ ነበር። ጽሁፉን ያነበብን ሰዎች ስንከራከር ተስፋዬ ሻዕብያ ነው የሚሉ አልጠፉም፡፡ ሌሎች ደግሞ የሻዕብያና የወያኔ ቅጥረኛ ነው ያሉም አሉ። ምን አገባው በኢትዮጵያ ፖለቲካ? የሚሉም ይገኙበታል።

እኔ ግን ኢትዮጵያዊ አይደለም በሚሉት አልስማማም ኢትዮጵያዊ ነኝ ካለ ማንም ሊከለክለው አይገባም። ግን ይህቺ ሃገር ጀግና ዜጎች እንዳሉዋት ሁሉ ለጠላት አድረው የቧረቦሩዋትም አሏት። ዋናው ጥያቄ ኢትዮጵያዊቱ ሳይሆን ዛሬ የቆመው ለማን ነው?

ያለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ውስጥ በወያኔ የተጀመረው የዘር የመከፋፈል ፖለቲካ እያከተመ የመሄዱ ጉዳይ ትንሽ ጭላንጭል የታየበት በመሆኑ ለኢትዮጵያውያን ደስታን፣ ለከፋፋዮች ደግሞ ንዴትን የጫረ ይመስለኛል ። ስለዚህም ሌላ የመከፋፈያ የጦር ግንባር መክፈት ለሻዕብያና ለወያኔ ቅጥረኞች አስፈላጊ ሆኖ ነበር።

የመንግሥቱ መጽሐፍ በነ ተስፋዬ አካባቢ የአማራና የኦሮሞ ጉዳይ እያከተመ እየሄደ በመሆኑ ኢትዮጵያውያ የመከፋፊያው የመበጥበጫው ማንካ (stirring spoon) መሆኑ የታመነበት ይመስላል። በተስፋዬ ገብረ አብ አነሳሽነት “ ኢ.ሕአፓን በመኢሶን - እሾህን በሾክ “ የሚል ርዕስ የወጣውን ጽሁፍ ስንመለከተው ሁኔታውን ፍንትው አድርጎ ያሳየናል።

ተስፋዬ ያላሰብነውን ሁለተኛ ግንባር በመክፈት በደንብ እንደከፋፈለን መሞከሩን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደብኝም። በድረ ገጾች ዞሬ፣ በፓልቶኮች የሚባለውን ሰምቼ የተረዳሁት በጣም የሚያሳዝን ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በተለይ ሻዕብያንና ወያኔን የሚደግፉ ሁሉ ይህንን አጀንዳ በማራገብ ላይ መሆናቸውን ስንመለከት ሃገራችን ያለባትን ችግር ለመረዳት አያዳግተንም።

ስንቱን የሻብዕያና የወያኔን የመከፋፋያ መንገድ አጋልጠን እንዘልቃለን ?

ስለ ተስፋዬ ገብረ አብ ዓላማ ለመረዳት እኔን ጨምሮ ብዙ ጊዜ የወሰደብን እንዳለን ሁሉ አሁንም ያልተረዱት እንደሚገኙ ጥርጥር የለኝም። የእሱን የመከፋፈያ ጽሁፍ ከፍ አድርገው የሚያስነብቡ፣ በእሱ ላይ የተጻፈውን ተቃውሞ የማያወጡ ድረ ገጾች እንዳሉ ከተረዳሁ ቆይቻለሁ። እውን የዚህ ግለሰብ ተንኮል

ሳይረዱት ቀርተው ነው? ለምንስ ብለው በአደባባይ ለሰጠው ቃለ መጠይቅ መልስ እንዲሰጥ አይጠይቁትም?

ከሁሉ የሚገርመኝ ቀደም ሲል በጽሁፉ ተስፋዬ የወነጀላቸውን ግለሰቦች ወደ ኋላ ተመልሰን እንመልከት። ስዬ አብርሃ፣ ነጋሶ ጊዳዳ . . . ። ምን የሚያመሳስል ሁኔታ አላቸው? ብለን ብንጠይቅ መልሱን በቀላል እናገኘዋለን። ከዘር ድርጅት ወጥተው ወደ ሕብረ ብሔር ድርጅት የመግባታቸው ጉዳይ ይሆን ይሆን? ስለዚህም ይሆን ተስፋዬ ጦርነቱን በሁለቱ ግለሰቦች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የነበረው? እስቲ አገላብጣችሁ ምን ይጽፍ እንደነበር ተመልከቱት ?

ለነገሩ ተስፋዬ ቂመኛ ነው። ቂሙን የሚወጣበትን መንገድ ቆይቶም ቢሆን ያገኛል። ታዲያ በማር ቀበባብቶ መርዙን ይለቀዋል። ይህንን በደንብ የምትመለከቱንት የነጋሶን መንገድ በሚል በዳንኤል ተፈራ የተጻፈውን መጽሐፍ ስታነቡ ነው ። ገጽ 181 እንመልከት፡ -

"ኢህአዴግ በ1983 ዓ.ም. ሀገሪቱን ሲቆጣጠር ከነማስታወቂያ ሚኒስተሩ ዲማ ነገዎ የመምሪያ ሃላፊዎች በሙሉ የኢሕአዴግ ታጋዮች ነበሩ። የፕሬስ መምሪያ ተስፋዬ ገብረአብ ፣ የቴሌቪዥን አማረ አረጋዊ ፣ የኢዜአ መዝሙር ፈንታ ፣ የኦሮሞኛ ፕሮግራም ሃላፊ ደግፌ ቡላ እና የኦሮሞኛ ራዲዮ ፕሮግራም ሱሌማን ደዴፎ ነበሩ" . . . .

"ታዲያ ባደረግነው ግምገማዎች አንዳንዶቹ የአቅም ፣ ሌሎቹ የሙያ ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የስነምግባር ችግር ነበረባቸው። ለምሳሌ ሙስናን መጥቀስ ይቻላል። ለዜና ሥራ አበልና መኪና ተመድቦላቸው እነሱ ማስታወቂያ ይሰራሉ። በሠራተኛው ላይ አምባገነን የመሆን ሌሎችም ችግር ይፈጥራሉ ። ሴቶች ያመናጭቃሉ ፣ በዘመድ ይሠራሉ። የአመለካከት ችግር ነበረባቸው። ለስሙ የኢሕአዴግ ነገር ያስቀድማሉ፣ የብሔሮችን መብት በተመለከተ ግን ትምክተኝነትንና ጠባብነትን የሚያራምዱ ነበሩ። በእነዚህ ምክንያት ሁሉም እንዲለቁ አድርገናል። ብዙዎቹ ወደ ኢሕአዴግ ተቋማት - ፋና ዋልታ ሲዛወሩ ተስፋዬ ገብረአብ ወደ እፎይታ መጽሔት ተልኮአል ። ከእነአካቴው እንዳይባበረሩ ደግሞ ሁሉም ታጋዮች ናቸው።"

ይህንን የነጋሶን መንገድ ላነበብን ዶክተር ነጋሶ ይዋሻሉ ለማለት አንደፍርም። በሌሎች እሳቸው ሊያስወቅሷቸው በሚችሉ አጀንደዎች ላይ ደፍረው ሲጽፉ እናገኛለን። ምን አልባት ወደፊት ጊዜ ከተገኘ የነጋሶን መንገድ የሚለውን መጽሐፍ ለመገምገም ይሞከራል። ለዛሬው ግን ዳንኤል ተፈራ በጥሩ ሁኔታ ተነባቢ አድርጎ ስላቀረበው ምስጋናዬ ይድረሰው።

ከዚህ የምንረዳው የዶክተር ነጋሶ ጊዳዳና የተስፋዬ ችግር የተነሳው በችሎታ ማነስና ለሥልጣን አለመብቃት ፣ ሙስናና ዝሙት ሆኖ ሳለ ተስፋዬ ግን ያንን ቂሙን ከስንት ጊዜ በኋላ አንስቶ ስንት የተሳሳተ መረጃ ሲከትበን እንደነበረ አስቡት። የነጋሶን አገላለጥ ስትመለከቱ ስዕብናን በሚያከበር መንገዱ ሃሳባቸው ሲገልጡ ታገኙታላችሁ ። ተስፋዬ ግን በጣም ወርዶ ስም እስከማጥፋት የሚደርስበት ሁኔታም አለ።

ዛሬ ተስፋዬ ለምን ሁለተኛውን የጦር ግንባር ለም ለማንሳት ተሯሯጠ ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል? እውነት ለኮፒ ራይት ነው? ወይስ ሌላ ቂም አለው። እኔ በበኩሌ ባለፉት ወራት የሞከረው ኦሮሞን ከአማራ የማጣላት ዘመቻ በተለይም ደራሲ አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስን በሚመለከት የሰጠው የተሳሳተ አሉባልታ በማያዳግም ሁኔታ መመታቱና አልፎ ተርፎም የኦሮሞ ነጻ አውጭን በሚመለከት ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል በመታየቱና በወያኔ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት ትግሉ ከቀጠለ የሚመጣውን ችግር ቀድሞ በመረዳት ሌላ ከፋፋይ አጀንዳ ይዞ ብቅ አለ ።

እውን ስብሃት ነጋ ስለኢሕአፓ አመሰራረት የሠጠው መረጃ ጠቃሚና እውነት ሆኖ ነው? ወይስ እርጅና የኢትዮጵያዊነት መለኪያ? ሁለቱም አይደለም። ተስፋዬ ሁለተኛውን ግንባር የከፈተው በኦሮሞ ድርጅት እየተካሄደ ያለው ለውጥ ለብዙ ዘመናት የዘራው የጥላቻ ዘመቻ ሲከሽፍበት አዲስ የመከፋፋያ አጀንዳ አንግቦ ነው። ስለ ኮፒ ራይት እንናገር ከተባለ ብዙ ማለት ይቻላል። ግን እሱም አይደለም። ለተስፋዬ የተሰጠው የቤት ሥራ የመንግሥቱን መጽሐፍ ወይም ዴሞክራሲን መከላከል ሳይሆን "አማራን በኦሮሞ ፣ ኢሕአፓን በደርግ ፣ እሾክን በሾክ ነው"። ይህንን ደግሞ ተስፋዬም አልካደውም ። ተስፋዬ የጻፈውን ተመልከቱት ፡ -

“መንገድ ላይ ወደሚገኘው ግሮሰሪ ሄድኩ። “እሾክን በእሾክ”፣ “ኢህፓን በመኢሶን”፣ ‘ብርድን በበረዶ”፣ እንዲሉ ቀዝቃዛ ቢራ አዘዝኩ “

እኔ ደግሞ ልቀጥልበትና፡ -

"አማራን በኦሮሞ፣ ስዬን በመለስ ፣ ኢሕአፓን በስብሐት ፣ ሽማግሌን በወጣት፣ ኢትዮ ሚዲያን በኢካዲኤፍ ፣ አሲምባን በከረንት አፌርስ" እያለ ሊቀጥልበት ይችላል። ተስፋዬ የማይነካው ሰው ቢኖር ኢሳያስ አፍወርቂን ብቻ ነው። ተስፋዬ ያልገባው ነገር ቢኖር ሁላችንም አራዶች መሆናችንን ነው። አራዳ ላራዳ ይታያያል ካብ ለካብ እንዲሉ።

ጽሁፉን ሲጀምር እንዲህ ብሎ ነው ፡ -

“ይህን አሳዛኝ ዜና የሰማሁት፣ ጥር 17፣ 2012 ተስያት ላይ ነበር።
አንድ ጓደኛዬ በስልክ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣

“ኢህአፓ የፈፀመውን ሰማህ?”
“አልሰማሁም። ምን ፈፀመ?”

ባጭሩ ነገረኝ።”

እኔ ደግሞ ልጨምርበት ።

“ኢህአፓ የፈፀመውን ሰማህ?” ብሎ ስብሃት ነጋ ደውሎ ጠየቀኝ ።

“አልሰማሁም። ምን ፈፀመ?”

“ የመንግሥቱን መጽሐፍ በኦን ላይ ለቀቁት እኮ “

“ ታዲያ ምን ይደንቃል “

“ ምን ማለትህ ነው ኢሕአፓን በኢሠፓ እናፋጃቸዋ ። የአማራና የኦሮሞ ጉዳይ እንደሆን እያከተመ ነው “

"ከስብሐት ነጋ የሚላክልኝን ነዋይ እያሰብኩ የማዘውን ቢራ ከአለ ሃሳብ ጨመርኩ።"

ስለ ተስፋዬ ከዚህ በላይ ማለት ባልፈልግም፣ ከልጅነቱ ጀምሮ በውስጡ ታትሞ የሚያብሰለስለውን ኢትዮጵያውያንን የመከፋፈል አባዜ በዚህ አጋጣሚ ከመሸገበት ጉድጓድ በአዲስ ቅኝት ይዞ ብቅ ማለቱ አያስደንቀኝም። ለነገሩ የአሁኑ አጀንዳ ሲከሽፍበት ምን አዲስ የመከፋፈያ አጀንዳ ይዞ እንደሚመጣ መገመት አይቻልም ። ሙሉ ቀን ለዚሁ ተቀጥሮ ሲጎነጉን ስለሚውል መጠበቅ ብቻ ነው። እኛም እንከፋፈላለን እሱም በእኛ ላይ ይሳለቃል።

የዋሆች መድረክ እየሠጣችሁት እንዲሳለቅብን የማታደርጉበት ቀንን ማየትን እናፍቃለሁ።

የሻዕብያና የወያኔ ሴራ ይጋለጣል!